በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
ቤተክርስቲያን ምስካዬ ኃዙናን ስደተኛው መድኃኔዓለም
ቤተ ክርስቲያን የጀርመን ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

Sekretariat der Äthiopisch-Orthodoxen
Tewahedo-Kirche in Deutschland Meskaye Hizunan
Medhanealem Exil Kirche Diözese Deutschland e. V

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አኃዱ አምላክ አሜን*

ታሕሳስ ፳፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.
Frankfurt am Main, 07.12.17

## ለኢትዮጵያውያን በሙሉ በያላችሁበት

***"ኑ ቤቴን ሥሩ እኔም በርሱ ደስ ይለኛል ይላል እግዚአብሔር" ት.ሐጌ ፩፣፰***

ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዲሉ በመድኃኔዓለም ቸርነትና መልካም ፈቃድ፣ በካህናትና ምእመናን ትብብርና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከረጅም ዓመታት ያላሰለስ ጥረት በኋላ እነሆ በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ እጅግ ግዙፍ ቤተ ክርስቲያንና ማእከል የሚሆን ሕንጻ መግዛታችንን በቅድሚያ ለመላው ኢትዮጵያውያን እናበስራለን፡፡

ይህ ቤተ ክርስቲያን አምልኮት የምንፈጽምበት ቅዱስ ቦታ ከመሆኑም በተጨማሪ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ደስታውንም ሆነ ሀዘኑን በጋራ የሚወጣበት፣ ሕጻናት ሃይማኖታቸውን፣ባህላችውንና ቋንቋቸውን የሚማሩበት በአጠቃላይ በውጭ ሀገር ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ቋሚ አድራሻና የሚያኮራ የታሪክ ቅርስ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ይህን ቤተ ክርስቲያን ለመግዛት ከነበረው ከፍተኛ ውጣ ውረድ ባሻገር ለብዙ ዘመናት ምእመናን ያዋጡትን ገንዘብ ባንኩ ምንም ሳያስቀር ከብድር ውላችን ጋር ስላሰበው በአሁኑ ወቅት ቋታችን ባዶ መሆኑን ለመግለጽ ተገደናል፡፡

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኑ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጥ ውስጣዊ ይዞታውን ማለትም መንበሩን፣ቤተ መቅደሱን፣ምንጣፉን፣የድምጽ ማጉሊያውን፣ወንበሮቹን፣ኤሌክትሪኩን፣ቀለሙንና አጠቃላይ እድሳቱን ወዘተ ለማሟላትና ወርሃዊ ዕዳውን ለመክፈል በርካታ ገንዘብ አስፈላጊ መሆኑ አይዘነጋም፡፡

በዚህም መሠረት ይህ ቤተ ክርስቲያን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ አድራሻ፣ ቅርስና ማእከል በመሆኑ ከሥር በተገለጠው የባንክ ቁጥርና አድራሻ ወይም በአካል ፍራንክፈርት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚችለውን ዕርዳታ እንዲለግስና የታሪክ አሻራውን እንዲያኖር ቤተ ክርስቲያን በመድኃኔዓለም ስም ጥሪዋን ታቀርባለች፡፡

**ማሳሰቢያ**

1. በሕግ የተቋቋመ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑ ታክስ ማስመለስ ይቻላል::
2. የከፈላችሁበት ደረሰኝ በአድራሻችሁ የሚላክ መሆኑን በአክብሮት እንገጻለን::

**የባንክ አድራሻ / Spendenkonto:**

Zahlungsempfänger : Ä.O.T.M.H.Medhanealem Exil Kirche
Verwendungszweck : Spende für Kirchenkauf
BANK: GLS Gemeinschaftsbank
IBAN : DE24 4306 0967 600 69157 00
BIC : GENODEM1GLS

Postfach 19 04 46
60091 Frankfurt/Main
Tel: 069- 27 29 50 22
Mobil: 0162- 19 77 3 18

Frankfurt Naspa Bank
Konto Nr. 14 10 86 154
BLZ: 51 05 00 15